# ኢሕአፓ ተሸንፏል ወይ ?

ተኮላ መኮንን

tekolamekonen@yahoo.com

እሩጫውን እየሮጡ እያለ ቀድመው እሩጫውን የጨረሱ አሉና መሮጣችሁን አቁሙ ማለት ትክክል አይመስለኝም ብል ይህንንና እርእሱን ምን አገናኘው ? የሚል ጥያቄ ይነሳ ይሆናል። ትክክለኛ ጥያቄ ነው። ለነገሩ ይህንን ጽሑፍ ለመጻፍ ያነሳሳኝ በአይጋ ፎረም ላይ **"እውነት ኢህአፓ አልተሸነፈምን? ደርግ-ኢሠፓስ?"** በሚል እርእስ በሲሳይ መንግስቴ አዲሱ http://aigaforum.com/articles/was-eprp-defeated.pdf የተጻፈውን ካነበብኩ በኋላ ነው። ጸሃፊው ስማቸው እውነተኛ የተጸውኦ ስም ነው ብዬ በማመን ወደ ትንተናቸው ልግባ። በመጀመሪያ ለጽሁፋቸው መንደርደሪያ የሆነው **"እሁድ ግንቦት 24 ቀን 2006 ዓ.ም ከስአት በኋላ በሚዩዚክ ሜይደይ ኢትዮጵያ አዘጋጅነት በብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጽሀፍት አጀንሲ የመሰብሰቢያ አዳራሽ የአሲምባ ፍቅር በተሰኘው መጸሀፍ ላይ ያተኮረ የግማሽ ቀን ውይይ ተካሂዶ ነበር፡፡"** የሚል ነው። ስለሆነም ዛሬ ስለመጽሐፉ ግምገማ የእኔን አመለካከት ለመግለጽ ባለማነሳቴ ስለዚያ ለመናገር ብቆጠብም መጽሐፉን አቤት ትረካ ብለው እንደ ወደዱት: አቤት ፍቅር ብለው እንዳነቡለት አለመሆኔን መደበቅ አልፈልግም። ምናልባት ወደፊት እንዳስፈላጊነቱ መዳሰስ እችል ይሆናል። መጽሐፉ የመወያያ መድረክ በመፍጠሩ ግን ከፋት የለውም ከሚሉት ድምር ነኝ። አቶ ሲሳይ የነበረውን ውይይት ሲያጠናቅሩ፥

**"በአጠቃላይም መጽሀፉ ስሜትን ኮርኳሪና ተአማኒነት ያለው ስራ ውጤት መሆኑ ተደጋግሞ የተወሳ ሲሆን የራያዎቹ ድላይ (የደራሲው ፍቅረኛ (እውነተኛ ስሟ ስመኝ) እና ይመር ንጉሴ የደራሲውን ህይወት በማትረፍ ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረከተ አርሶ አደር) መጸሀፉ እንዲህ እንዲወደድና ምሉዕ እንዲሆን በማድረግ ረገድ የነበራቸው ሚና ጎልቶ የወጣበት ኢጋጣሚ ነበር፡፡"**ይላሉ። ታዲያ የድላይ ፍቅር እውነት የነበረ ወይ ? ወይንስ ለማጣፈጫ የገባ ነው ? እውን በኢሕአሠ ታሪክ ወንድና ሴት ደክሚችኋልና ሂዱና እረፉ የተባለበት ወቅት ነበረ ወይ ? ድላይ ንፋስ የሚያውለበልበው ፊቷን የሚሸፍን ጸጉር ይዛ ታገለች ወይንስ እንደ ወንድ ተከርክማ ኮፍያ ከራሷላይ ሳይለያት ተሰዋች ? ይህና ሌላም ብዙ ጥያቄ ወደፊት የሚነሳ ይሆናል ብዬ በመጠቆም ወደ ተነሳሁበት ልመለስ።

ደራሲው የውይይቱ ተሳታፊዎች አዎ ኢሕአፓ ተሸንፏል ብለው መደምደማቸውንና ድርጅቱ ግን አልተሸነፍኩም ማለቱ ድክመት መሆኑን ነግረውናል። ኢሕአፓ አልተሸነፈም ማለት እንዴት ይቻላል ? ብዬም እኔም ከሳቸው ጋር ልስማማ። ቢያሸንፍ ኖሮማ ኢዮበልዩ ቤተመንግሥት እናየው አልነበር ? መሸነፉን ድርጅቱም ተቀበለም አልተቀበለም እውነታው በገሃድ የሚታይ እኮ ነው። ነገሩ " ትግሉን አልተውንም አሁንም እየታገልን ነው" ካሉ ያላቸውን የአባላት ብዛት የትግል መንገዳቸውንና ያደረጃጀት ብቃታቸውን የሚያውቁት እነሱ ናቸውና እንቀበል። የሉም ጠፍተዋል ለማለት ደግሞ የማያስችል ብዙ መጥቀስ ይስለሚቻል። ታሪክን የሚጽፍ አሸናፊ ነውና የሚጻፍ ታሪክ የላቸውም ተሸንፈዋል እንዳንል እንጠንቀቅ። ሁሉም በሂደት የሚታይ ነውና። "ልጅ ከሆነ ይወለዳል ሽል ከሆነ ይወርዳል" ይባል አልነበር።

እስከ **(እስከ 1983 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ በአያልነሽ ይመራ የነበረው የኢህአፓ ጥቂት የታጠቀ ቡድን ጎጃም ውስጥ በጃዊ፣ በአቸፈርና በጣና በለስ አካባቢ እንዲሁም ጎንደር በቋራ አካባቢ ይንቀሳቀስ እንደ ነበር ሳይዘነጋ)** የኢሕአፓ ሽንፈት በጎጃም ተጠናቀቀ ብለው የሚነግሩን ጸሐፊ አዋጊ የነበረች ያንዷት ታጋይ የጦር መሪ ስም ብቻ ይጠቅሱና ያልፋሉ። እዚህ ጋ ስደርስ ጸሃፊው የሌሎችን በወቅቱ የተያዙና እስከዛሬ ድረስ የደረሱበት ያልታወቀ፣ ቤተሰቦቻቸው አልቅሰው እርማቸውን ያላወጡባቸው የኢሕአፓ መሪዎች ሥም ጠፍቷቸው ሳይሆን እያወቁ የሚያመጣውን ወቀሳ በመፍራት ያለፉት እንደ ሆነ ገባኝና ትችታቸው የልብ እንዳልሆነ አድርጌ ወሰድኩት። ጸሃፊው ኢህአፓ ለምን ሳያሸንፍ ቀረ ለሚለው ያነሱት ነጥብ ከእውነታ ያልራቀ ቢሆንም አንዳንድ የሚያጠያይቁ ነገሮችን በነቃ ሕሊናቸው ሊያሳምኑን ሞክረዋል ። አንዱን እንዴው ለናሙና ልጥቀስ

**“ የኤርትራ ጉዳይ የነጻነት ጥያቄ ስለሆነ ሰላማዊ በሆነ መንገድ መፍትሄ ይሰጠው፣”** አለ ኢሕአፓ ይላሉ። እንዴው ስለእውነት እናውራ ኢሕአፓ እንዲህ ብሎ ነበር ? አላለም ። የብሔር ጥያቄ በዲሞክራሲያዊ መንገድ ይፈታ ብሏል ። የኤርትራ ጥያቄ በሰላማዊ መንገድ ይፈታ ብሏል። የነጻነት ጥያቄ ነው ግን አላለም። እንዴውም ከኤርትራ ታጋዬች ጋር የነበረው ጥል ድርጅቱ ያንን ባለማለቱ ነበር። የነጻነት ጥያቄ ነው ካለ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው ብሎ መቀበል ስለሆነበት ባቋሙ ጸንቷል ። ድርጅቱ ምን ግዜም የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው ብሎ አያውቅም።

በተረፈ ኢሕአፓ የንኡስ ከበርቴው ቡድን አብራክ ነበር ማለት ትክክል ቢሆንም ደርግን ያሸነፈውና በድል አድራጊነት አዲስ አበባ የገባው ቡድንም ካገራችን ከትግራይ ውጡልን እናንተ **“አባይ ኢትዮጵያ ናችሁ”** ለትልቁ ኢትዮጵያ የምትታገሉ ናችሁ ሲሉ የነበሩትም እንዲሁ የንኡስ ከበርቴው አባላት መሆናቸውን እኔም ልስማማ። ነገር ግን በኢሕአፓ ፕሮግራም አምነው ለሶሺያሊስት አብዮት እርእዮተ አለም ትግል ሲሉ እራሳቸውን በድፍረት አሳልፈው የሰጡ ቆራጦች ብዙሃን ለመሆናቸው ጸሃፊውም ነካክተውታልና እኔም አስምሬበት ልለፍ። በእኔ እምነት በዚያን የትግል እሳት ውስጥ ያለፈ በሕይወት የሚገኘው ባብዛኛው ንቃትን፣ አርቆ አሳቢነትን፣ ጨዋነትን፣ እሩህሩህነትን፣ ለፍትሕ ተቆርቋሪነትን፣ ለአላማ መሰዋትን፣ እንደ መርህ የወሰደና በቀን ከቀን ኑሮው ላይ ለማንጸባረቅ የሚሞክር አሁንም ታጋይ ነው። ታጋይ ለመሆን እኮ የግድ ብረት መጨበጥ የለበትም።

ጸሃፊው ተሳታፊ የነበሩት ወጣቶች “ስለራሳችሁ ድርጅት ገድል ብቻ ነው የምታወሩት” ብለው ጥያቄ አንስተው ነበር ብለው ሲተርኩ **“በዚህም ሀሳብ መነሻነት አንዳንድ ወጣት ተሳታፊዎች ለምን የዚያ ትውልድ ሰዎች ሽንፈታችሁን በጸጋ ተቀብላችሁ ለዚህኛው ትውልድ አዎንታዊ ትምህርት ሊሰጥ በሚችል መልኩ ሀሳባችሁንና እውነተኛ እምነታችሁን አታቀርቡም? ለራሳችሁና እናትነተው ብቻ ለተሳተፋችሁበት የትግልና የአመጽ እንቅስቀሳሴ የምትሰጡት ግምትና ለአሁኑ ትውልድ ያላችሁ አተያይ ሚዛኑን የጠበቀ ነውብላችሁ ታምናላችሁን? እንደኔ እንደኔ በራሳችሁ ገድል ብቻ ታጥራችሁ የሌላውን ተሳትፎ ለማቀጨጭ ጥረት እያደረጋችሁ ያላችሁ ይመስለኛል የሚሉ ጥያቄ አዘል አስተያቶች ተሰነዘሩና ውይይቱ አሁንም ነፍስ ዘርቶ ቀጠለ፡፡”** ይላሉ። አባባሉን እንዳለ በግርድፉ ሲያስተውሉት እውነት ቢመስልም ማንም ሰው አብራርቶ መናገር የሚችለው ስለነበረበት ስላለፈበት እንጂ ስለሌላው ሊሆን አይችልም። ያንን ማድረግ የሚችለው የተለያዩትን ድርጅቶች ታሪክ አጠናቅሮ ማቅረብ የሚችለው ታሪክ ተራኪ፣ ወይንም ጋዜጠኛ መሆን ይኖርበታል። ካልሆነም ያንን የመመርመር ያሁኑ ወጣት ሚናም ነው። የነበረውን ለመቃኘት አሁን ብዙ እየተጻፈ ነውና። ለምን ጥፋታችሁን ሽንፈታችሁን አትቀበሉም ? ለሚለው አንድም ካደግንበት ባህል፣ ካልሆነም ከሚያስከትለው ሃላፊነት፣ ካልሆነም ከትችት ፍርሃት የመነጨ ይመስለኛል። እንኳን ይህንን ሚስቶቻችንን እንኳን መውደዳችን እንዳይታወቅብን የምንፈራ ሰዎች ነን።

ሌላው ሳላነሳ የማላልፈው የደርግን የቀይ ሽብር ተዋንያን ከኢህአፓ ጋር መደባለቁን ነው። ይህን ማድረግ የረገፈውን የወጣት ደም ደመ ከልብ ከማድረግ አልፎ የበሬና ያራጁን ታሪክ ማደባለቅ እንዳይሆን ይታሰብበት። ወንጀለኛነቱ ታውቆ የተፈረደበት ነፍሰ ገዳይንና ታጋይን ማመሳሰል ቢያንስ በጸሃፊው ላይ ትዝብት እንደሚያስከተል ልጠቁም። መፈታት ያልነበረበት በምሕረት ተፈቶ ሲታሰር ያመነውን ወንጀል ከእስርቤት እንደወጣ ክዶ ሲጽፍ መወንጀል የነበረበት ነበርና የእሱን መጽሃፍ ጠቅሰን ለመከራከሪያ ካመጣነው የውይይታችን ሂደት ወደ እማይሆን አለመስማማት ሊወስደን ነው። የቀይ ሽብር ተዋንያን የነበሩ ዛሬ አንቱ ለምን ተባሉ ለሚለው "እንግዳ ባደረ በዋለ ቁጥር ያረፈበት ቤቱ ይመስለዋል" እንዲሉ እነሱም በምህረት ሲፈቱ መታሰራቸውን የዘነጉ ይመስለኛል። ካልሆነ ጥፋተኛ ነን ያልነው ውሸታችንን ነው ያሉም ይመስላል። ለምን ቢባል ? 17 ዓመት በሬዲዮና በቴሌቪዥን ያደነቆሩንን ዛሬ በመጽሐፍ ሲበትኑልን መቀበላችንን ስላዩ ማለቴ ነው። "የሚገርመው የተናጋሪው ሳይሆን ያዳማጩ" እንደሚሉት ጥፋቱ የራሳችንም ጭምር ነው።

**በመጨረሻ ላይ ጸሃፊው "ኢህአፓ ያነሳቸው ጥያቄዎች በቀድሞው የኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኢህዴን) በአሁኑ ብአዴን /ኢህአፓ ውስጥ ሲታገሉ የነበሩና ኢህአፓ መፈራረሱ እርግጠኛ መሆኑን አስቀድመው የተገነዘቡ የበለሳው ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (የእርማት እንቅስቃሴ) አባላት የመሩት ቡድን አሁንም ቢሆን መታገል ይቻላል ብለው ህወሀት ይቆጣጠረው ወደ ነበረውና ተክራርዋ በመባል ወደ ሚታወቀው የትግራይ መሬት በመሄድ 35 ወንዶችና 2 ሴቶች በድምሩ 37 ወጣቶች በመሆን የመሰረቱት የፖለቲካ ድርጅት ነው/ እና በህዝባዊ ወያኔ ሀርነት ትግራይ (ህወሀት) አማካኝነት ከግንቦት 20/1983 ዓ.ም ጀምሮ ምላሽ እንዲያገኙ ጥረት እየተደረገ ነው በማለት የሚከራከሩ ወገኞች አሉና ለእነዚህስ ሰዎች መልሳቸው ምን ይሆን? እንግዲህ ሰው ያለውን ከወረወረ ፈሪ አይባልም ነውና ነገሩ እኔ ይህን ለማለት ሞክሬያለሁና እስቲ በጉዳዩ ላይ እንወያይበት፡፡"** በማለት ጥያቄ በማቅረብ ይደመድማሉ። እንዴው እኔም እንደ እሳቸው እርስዎስ ምን ይመስልዎታል ? ብላቸው መልሳቸው ምን ይሆን ? እኔ ልል የፈለኩት <u>በህወሀት አማካኝነት</u> ሲሉ ምን ለማለት ነው ? የነሱን ትግል ለማኳሰስ ነውን ? ጌታዬ በእኔ እምነት በኢትዮጵያ የተወለደ ሁሉ እኩል ኢትዮጵያዊ እንደሆነ ሁሉ ማናቸውም ድርጅት እንደ ድርጅት የከፈለውን መስዋእትነት እንዲሁ ሳላዳላ በእኩልነት እየተቀበልኩ ያሉና የነበሩ ልዩነትን በማጥበብ ለወደፊት አብሮ ለመስራት የሚችሉበትን መንገድ መፈለጉ ተገቢ ይመስለኛል። ማንም ይሁን ማን የራሱን ሕይወት አሳልፎ የሰጠው ካለፈው የተሻለ ስርአት ለመመስረት እንጂ አገርን ለማጥፋት አልነበረም። የማንም ድርጅት ታዛዥ ለመሆንም ነው ብዬ ስለማላምን ነው። "ብትር የያዘ ሁሉ አይነስውር ነወይ" ሲሉን ከሆነ የተነሱት ባረማመዱ መለየት ይቻላል ልበልዎትና ልደምድም። ለሰላምና ለዲሞክራሲ፣ ለእኩልነትና ለፍትሕ፣ ተለያይቶ ለመወያየት ተወያይቶ ለመቀራረብ፣ በሃሳብ መለየትን እንደ ጠላትነት ላለመቁጠር እንታገል። በመድረሻው ከተስማማን በመንገዱ አንጣላ። ልበልና ላሳርግ።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር